Mon, july 8, 2013

**የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤ/ክርስቲያን የሥራ እንቅስቃሴ አጭር ሪፖርት**

ሰሞኑን ለ3 ተከታታይ ቀናት በዎጅና ደብረሲና ቤ/ክርስቲያናት የሚደረገውን የሥራ ዕንቅስቃሴ ለመገምገም በመስክ ጉብኝት ላይ ነበርኩ። በሁለቱም ፕሮጄክቶች በእጅጉ የሚያመረቃ ሥራ ተከናውኖ ተመልክቻለሁ።

**ደብረሲና፡** የቤተ/ክርስቲያኑ ቅጥር ዙሪያውን ተክቦ አልቋል። በርግጥ የካቡ ቁመት ገና መቀጠል ይኖርበታል። የአጥሩ ዙሪያ በመግጠሙ ግን በጣም ተደስቻለሁ። ልክ እንደ ዘሃራ ቤ/ክርስቲያን መግቢያ በር (ዕድሞ) መሰራት እንዳለበት ከሚመለከታቸው ጋር ተመካክረናል።

**ዎጂ፡** በዚህ ፕሮጄክት የተመለከትኩት የሥራ እንቅስቃሴ ከጠበቅሁት በላይ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። በመሆኑም ግምቱ ቀላል ነው የማይባል መሬት ተመልሶ በቤ/ክርስቲያኑ ክልል ተካቷል። የአካባቢውን ህብረተሰብ ስምምነት መሠረት በማድረግ ህገወጥ የቤት ግንባታዎች እንድፈርሱ ተደርጓል ። በአሁኑ ጊዜ 80 በመቶ የሚሆነው አጥር ከፍታ 70 ሴሜ ነው። በዚህ ዓመት የቤ/ክርስቲያኑን ይዞታ የመከለል እንቅስቃሴ ቅድሚያ የተሰጠው ሲሆን በመጭው ዓመት ደግሞ የአጥሩን ከፍታ ለመጨመር ዕቅድ ተይዟል።

በአሁኑ ሰዓት የክረምቱ ወራት ስለባተ የዘር ወቅት ነው። ስለሆነም ገበሬዎች በሥራ ተጠምደዋል። ነገር ግን እስካሁን ባደረጉት የሥራ እንቅስቃሴና አካሄድ በጣም ረክቻለሁ። በቤ/ክርስቲያኑ ቅጥር ግቢ የቤት እንስሳት ስምሪት ከተከለከለ ወዲህ የቤ/ክርስቲያን ደኖች መሻሻል እየታየባቸው መጥቷል።

በመጨረሻ በኢትዮጵያ የኦርቶዶክስ ቤ/ክርስቲያን ደኖች ላይ ተጨባጭ ለውጥ ማሳዬት በመጀመራችን በእጅጉ ተደስቻለሁ። ይህ ሁሉ ሊፈጸም የቻለው ደግሞ በTree Foundation ያላሰለሰ ጥረት መሆኑን መጠቆም እወዳለሁ።

አመሰግናለሁ።

ዓለማየሁ ዋሴ (ዶ/ር)